

# በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ምእመናን ጉባኤ

**የእግዚአብሔር አብ ጸጋ ፤ የእግዚአብሔር ወልድ ቸርነት ፤ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም አንድነት በሀገራችን በኢትዮጵያና በሕዝብዋ ላይ አድሮ ይኑር አሜን**

**ከልዩ ልዩ የአሜሪካ ስቴቶች ቤተ ክርስቲያኖቻቸውን ወክለው የመጡ ካህናትና ምእመናን ፤ እንዲሁም የአስተናጋጁ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ፤ የቦርድ አባላትና የሀገር ሽማግሌዎች ከሚያዝያ ፳፭ እስከ ሚያዝያ ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በሚኒያፖሊስ ሚኒሶታ ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በወቅታዊ የቤተ ክርስቲያናችንና የሕዝባችን ችግሮች ላይ ያተኮረ ታላቅና ታሪካዊ ጉባኤ አድርገዋል ፤ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን የጋራ መግለጫም አውጥተዋል።**

## ***የጉባኤው የጋራ መግለጫ ከነማሳሰቢያው***

**በቅዱስ መጽሐፍ *"ለሁሉም ጊዜ አለው ለጸብ ጊዜ አለው ለሰላምም ጊዜ አለው"* ተብሎ ቢነገርም ሰላሙን ወደጠብ ፤ ጠቡንም ወደ ሰላም መለወጥ የሚችሉ ግን በእግዚአብሔር አርአያና አምሳል የተፈጠሩ ሰዎች ብቻ ናቸው።**

**በሁሉም ዘንድ እንደሚታወቀው:-**

**-አሁን ያለንበት ዘመን የሰላም ዘመን ሳይሆን ሰው ሁሉ ሳይጣላ ተጣልቶ የተኮራረፈበት ዘመን ነው ፥**

**-አሁን ያለንበት ዘመን ሐሰተኞች የእሾክ አክሊል ጎንጉነው በእውነት ራስ ላይ ደፍተው "ስቅሎ ስቅሎ" (ስቀለው ስቀለው) እያሉ በመጮህ እውነት በዕፀ መስቀል ላይ ተቸንክሮ እንዲሰቀል እያደረጉ ያሉበት ዘመን ነው ፥**

**-አሁን ያለንበት ዘመን እውነት በመስቀል ላይ ተሰቅሎ *"አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ"* እያለ የሚጮህበት ዘመን ነው ፥ ይህንንም ጩኸት ሰምተው እውነት በተሰቀለበት ዕፀ መስቀል ሥር የሚገኙት እውነተኛ ሕሊና ያላቸው ነፍሳት እንጂ በሐሰተኞች የሐሰት ስብከትና ፕሮፓጋንዳ የተጠመቁትማ እውነት በመስቀል ላይ ውሎ እንዳያድር ጭኑን ሰብረው ያም ባይሆን ደግሞ ጎኑንን በጦር ወግተው ለመቅበር እየተጣደፉ ናቸው።**

የገለልተኞች አብያተ ክርስቲያናት ካህናትና ምእመናን ጉባኤ ከተቋቋመባቸው ዐበይት ምክንያቶች አንዱም የእውነትን ጩኸት በመስማትና ከመስቀሉም ሥር ሆኖ እውነትን ለመመስከር ነው ፤ ይህም ማለት ከአንዲት ኢትዮጵያ አካል ላይ ጠመንጃ ጨብጦ መገንጠልና ከአዲት የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንም ላይ መስቀል ጨብጦ መገንጠል በይዘቱም ሆነ በሂደቱ ተመሳሳይ መሆኑን በማመን መገንጠልን ለመቃወም ነው ፤ በተለይም አባቶች የራሳቸውን ክብር ከቤተ ክርስቲያን ክብር በላይ አድርገው በመገመት የወሰዱትና የሚወስዱትም እርምጃ ለሀገር አንድነት ምሳሌነቱ የከፋ መሆኑን ሕዝቡ አርቆ የማስተዋል አእምሮ ተሰጥቶት እንዲገነዘበው ለማድረግ ነው ፤ በመጨረሻም አሁን በዚህ በሁለት ሺሕ ዓመታት ፍጻሜ ላይ እውነትን ፣ ፍቅርን ፣ ሰላምንና አንድነትን ለተጠማችው ቤተ ክርስቲያናችን ተገዳ እንድትጠጣው በሰፍነግ ተሞልቶ የቀረበላት የታሪክ ኾምጣጤ  መራራ መሆኑን "**ጆሮ ያለው ይስማ**" በማለት እውነትን ለማሰማት ነው::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ገና ከመሠረቱ ጀምሮ የጵጵስናን ሢመትና የፓትርያርክነትን ማዕርግ ባለቤትነት በተመለከተ በግብፃውያን የውሸት ማነቆ ታንቃ ፣ በተንኰል ልጓም ተለጉማ ለ፩ ሺሕ ፮፻ (1600) ዓመታት ያህል ስትፈተን የኖረች ቤተ ክርስቲያን ናት።
ታሪኩም ባጭሩ እንዲህ ነው:- በአሁኑ ጊዜ በቱርክ ግዛት ውስጥ በምትገኘው "ኒቅያ" ተብላ ትጠራ ወደነበረችው ከተማ በንጉሥ ቆስጠንጢኖስ ጋባዥነት የገሰገሱት ፫፻፲፰ (318) ሊቃውንት ታላቁን ጉባኤ (ሲኖዶስ) ያደረጉት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ፫፻፳፭ (325) ዓ.ም ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በጳጳስ ደረጃ የተቋቋመችው አሁንም እ.አ.አ. በ፫፻፳፰ (328) ዓ.ም ነው። የኒቅያ ጉባኤ አርዮስን ያወገዘ ጉባኤ ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያን የምትተዳደርባቸውን ሕጎችም በሚገባ የደነገገ ጉባኤ ነበር ፤ ነገር ግን እነዚያ መንፈሳውያን አበው በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው በደነገጉት ፍትሕ መንፈሳዊ ላይ የሥልጣን ልክፍት የተጠናወታቸው የግብፅ ጳጳሳት በንጹሕ ልብ የቀረባቸውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመሸፈጥ ሲሉ በኒቅያ ጉባኤ (ሲኖዶስ) የተደነገገ ድንጋጌ በማስመሰል ወደ እነርሱ ቋንቋ በተተረጎመው የጉባኤው ውሳኔ በአንቀጽ ፬ (4) ክፍል ፵፪ (42) ላይ ***"የኢትዮጵያ ሰዎች ከአዋቂዎቻቸው ወገን በራሳቸው ፈቃድ ጳጳስ መሾም አይችሉም"*** ብለው ሥርዋጽ (ዲቃላ) ሕግ በመጨመር በሐሰት ሰንሰለት ሕዝባችንን አስረው ዐይነ ሕሊናውንም አሳውረው ቤተ ክርስቲያናችንን በተንኰልና በሐሰት ሲገዙ ኖረዋል።

እኛም አሁን ቤተ ክርስቲያን ተሰዳለች ፣ ሲኖዶስዋም ተሰዶአል ፣ መንበርዋም ተሰዶአል የሚሉትን ወገኖች የምንቃወምበት ዋና ምክንያት ስልታቸው ልክ እንደ ግብፃውያን በንጹሕ ልብ የተከተላቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በቃል በሚናገሩትና በጽሑፍ በሚበትኑት የሐሰት መልእክታቸው ሥርዐተ ቤተ ክርስቲያን የፈረሰ ፣ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን የተጣሰ እያስመሰሉ  ለግል ክብራቸውና ጥቅማቸው ሲሽቀዳደሙ ለዘመናት በአንድነቱ ጸንቶ ፥ በሃይማኖቱ ፣ በታሪኩ ፣ በባህሉ ኮርቶና ተከባብሮ ፥ በክፉም ሆነ በደግ ጊዜ ሳይለያይ ተዋዶ ፣ ተጋብቶና ተዋልዶ የኖረውን የኢትዮጵያን ሕዝብ እንዳይበታትኑት በመስጋት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትናንትም ዛሬም ነገም ያው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ፤ ዛሬ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንጨነቅለታለን እናስብለታለን የሚሉት ትናንት በሥልጣኑ መንበር ላይ ተንሰራፍተው በነበሩበት ጊዜ "***ኢትዮጵያ ትቅደም አድኃሪ ይውደም***" የሚል

የአብዮት መፈክር እያስተጋቡ ከአረጋዊው ንጉሠ ነገሥት እስከ ፓትርያርኩ ፥ ከመሳፍን ቱ ፣ መኳንንቱ ፣ ጀኔራሎቹ ጀምሮ በትምህርት ገበታ ላይ እስከ ሚገኘው ወጣት ድረስ በግፍ ሲጨፈጭፉት የተጮኸው ጩኸት ፣ የተፈጸመው ሰቆቃ እንደ ራሔል እንባ እስከ ራማ ድረስ ሲሰማ እነርሱ ሳይሰሙቸው የአብዮት ፕሮግራም አራማጆች የነበሩ ሰዎች ዛሬ እንዴት ለሕዝብ ብሶት አሳቢዎችና ተቆርቋሪዎች ሊሆኑ ቻሉ?
ቅዱስ ዳዊት በመዝሙሩ "***ህየ ይወድቁ ኩሎሙ ገበርተ አመፃ ይሰደዱ ወኢይክሉ ቀዊመ _ ክፉ ወንጀልን የሚሠሩ ሁሉ ይወድቃሉ መሸሸ እንጂ መቆም አይችሉም***" ብሎ የተናገረው ትንቢት በተናንትናዎቹ ላይ እንደ ተፈጸመ የዛሬዎቹም የሕዝብን ብሶት ለመስማት ጆሮ ዳባ ልበስ ካሉ ትንቢቱ የሚፈጸምበት ጊዜ ይመጣል::
እግዚአብሔር ለሁሉ እንደ ሥራው የሚከፍል አድልዎ የሌለበት እውነተኛ ዳኛ ነውና።

## <u>የአቅዋም መግለጫ</u>

፩. የበላይ ማነው? ሲኖዶስ ወይስ ፓትርያርክ የሚል ጥያቄ ለጉባኤው ቀርቦአል ፤ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያኒቱ ሁለንተናዊ አመራር ሰጪ ፣ የቤተ ክርስቲያኒቱ ራስ ፣ ምሶሶና ዋልታ ፣ መሆኑንና ፓትርያርኮችም  የሚወጡት ወይም የሚመረጡት ከሲኖዶሱ አባላት ወይም ከገዳም አበ ምኔቶች መሆኑን ገልጾ ጉባኤው መልስ ሰጥቶበታል።

፪. ሕጋዊና ሕጋዊ ያልሆነ ሲኖዶስ ለሚባለው አነጋገር የሚሰጠው ትክክለኛ ማስረጃ ምንድን ነው? ተብሎም ለቀረበው ጥያቄ:-
ሕጋዊ ሲኖዶስ የሚባለው ከመጀመሪያው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ጊዜ ጀምሮ ሲያያዝ የመጣው ሲኖዶስ ብቻ ነው። ይህም ሲኖዶስ አባላቱ በሞት ፣ በሽሽት ፣ ወይም በሌላ ምክንያት እስካልተለዩት ድረስ ቀድሞም የነበረው ፣ አሁንም ያለው ፣ ወደፊትም የሚኖረው የታቦተ ጽዮን መዲና በሆነችው ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ብቻ መሆኑን ጉባኤው በአጽንኦት አስምሮበታል።

፫. ፓትርያርክ በሕይወት እያለ ሌላ ፓትርያርክ ስለ ተሾመ ቀኖና ፈርሶአል በሚል ጭፍን ስብከት ብዙ ምእመናን ግራ ተጋብተዋል ፤ እውነቱ ምንድን ነው? ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ መልስ ይሆን ዘንድ የታሪኩን ሂደት ጉባኤው ከዚህ ቀጥሎ አቅርቦታል።

ኃይልና አመፅን በመጠቀም በኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወትና ንብረት ላይ የፈለገውን ያደርግ የነበረውና አምላከቢስ የሆነው የደርግ ሸንጎ አባልና የአብዮት ፕሮግራም አራማጅ በመሆን የታወቁት አራተኛው የቀድሞው ፓትርያርክ የደርግ ሥርዐት ከወደቀ በኋላ በሕመም ምክንያት ኃላፊነቱን ሊሸከሙ አለመቻላቸውን ለሲኖዶሱ አቅርበው ሥልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለቀቁ። በወቅቱ እንደራሴያቸው የነበሩና አሁንም ተሰዶአል የሚሉት ሲኖዶስ አባል የሆኑት አባት የመሪነቱን ቦታ ይዘው ሲኖዶሱን በሊቀ መን በርነት ለመንፈቅ ያህል ሲመሩ ቆዩ ፣ የፓትርያርክነቱንም ቦታ ለማግኘት ትልቅ ዘመቻ አድርገው ነበር ፤ ግን ሁኔታው እንዳሰቡትና እንደ ተመኙት ሆኖ ባለመገኘቱ ሀገር ለቀው ወጥተዋል ፤ አሜሪካ እንደገቡም በፓትርያርክ ላይ ፓትርያርክ ተሾመ ፣ ቤተ ክርስቲያን ተሰደደች ፣ ሲኖዶስም ተሰደደ ፤ ይህም በመሆኑ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተጣሰ የሚለውን ደረቅ የማደናገሪያ ስብከት ማሰራጨት ጀመሩ ፣ እንግዲህ በዚህ መልኩ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን ተጣሰ ቢባል እንኳ የጣሱት እነዚሁ አሁን እዚህ አገር

ያሉ አባቶች ራሳቸው መሆናቸውን የታሪክ ሂደቱ በግልጽ ያሳያል። ከዚህም በላይ የዐይን ምስክር የሆኑ አበው ሊቃነ ጳጳሳት ፣ ካህናትና ምእመናን አሉ ፣ የጽሑፍም ማስረጃዎች ይገኛሉ ፤ በተለይም የቀድሞው ፓትርያርክ በፈቃዳቸው መውረዳቸውን ገልጾ በነሀሴ ወር ፲፱፻፹፫ (1983) ዓ.ም የወጣውን የቤተ ክርስቲያን ልሳን ድምፀ ተዋሕዶ ጋዜጣን በመጥቀስና ለጉባኤው አባላት ቅጂውን በማቅረብ ጉባኤው መልስ ሰጥቶበታል።

፬. ገለልተኛ ነን ስንል ምን ማለታችን ነው? ለሚለው ጥያቄም ገለልተኛነታችን በምንገኝበት ክፍለ ዓለም የሀገሩ መንግሥት ሕግና ስለ እምነት ተቅዋሞች የሚከተላቸውን መመሪያዎች ባገናዘበ መልኩ በተዘጋጀው የየቤተ ክርስቲያኑ የውስጥ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ያለቤተ ክህነት ተጽእኖና ጣልቃ ገብነት በነጻ የውስጥ አስተዳደር በመመራታችን ነው እንጂ በሃይማኖትና በቀኖና የአንዲትዋ ቤተ ክርስቲያናችን አካል ነን። አንዲትዋ ቤተ ክርስቲያናችን ስትከፈልና ቀኖናዋ ሲፈርስም ዳር ሆነን አናይም ፤ መከፈልን መገንጠልን በጽኑእ እንቃወማለን ፤ በአንጻሩ ደግሞ የቤተ ክርስቲያናችን ቅዱስ ሲኖዶስ፦

- በተዛባ አመራር ምክንያት አብያተ ክርስቲያናት ሲታመሱና ሲተራመሱ
- አብያተ ክርስቲያናት ሲቃጠሉ ፣ ሲፈርሱ ፣ ሲዘጉና ንዋያተ ቅድሳት ሲመዘበሩ
- ካህናትና ምእመናን በገዛ አገራቸው በሃይማኖታቸው ምክንያት በአክራሪ እስላሞች ደማቸው በሰማዕትነት ሲፈስ
- እስልምናን በከፍተኛ ፍጥነት በሀገሪቱ ለማስፋፋትና በክርስትናው ሕይወት ላይ ለማጥላት ሀብታሙ በገንዘብ ፣ ምሁሩ በዲፕሎማሲ ፣ አክራሪው በጎራዴ ተሰልፎ ኃይል የተላበሰ ግስጋሴ ሲደረግ
- መናፍቃን የጳጳሳትን የሥልጣን ሽኩቻና የመለያየት ሁኔታ እንደ መረጃ እየጠቀሱ መንጋውን ከቤተ ክርስቲያን ሲማርኩ ምንም ነገር እንዳልተደረገ ተቆጥሮ በዝምታ መታለፉ እጅግ አሳዝኖናል ፤ በሃይማኖታቸው ምክንያት ሰማዕትነት ተቀበለው ለሞቱትም በአገር አቀፍ ደረጃ ጸሎተ ፍትሐት ባለመደረጉ ልባችን በኃዘን ፍላፃ ተነድፎአል ፤ በተጨማሪም በልማዱ እንደቆየው ከፍተኛ በደል የፈጸሙ ሰዎች እንኳ የቤተ ክርስቲያንን ደወል ደውለው ምሕረት እን ዲደረግላቸው ፣ ዕርቅ እንዲወርድላቸው ሲማጸኑ ቤተ ክርስቲያን ትማልድላቸዋለች ፣ ታስታርቃቸዋለች ፤ በጊዜአችን ግን ይህንኑ ሃይማኖታዊ ልማድ ተከትለው ቤተ ክርስቲያንን የሙጥኝ ያሉትን ከቅጽረ ቤተ ክርስቲያን አስወጥቶ በር መዝጋትና ወገኖችን ለሸሹት ችግር አሳልፎ መስጠት ከቤተ ክርስቲያን የማይጠበቅ አሳዛኝ ድርጊት ነው ፤ አሁንም ቢሆን ቅዱስ ሲኖዶስ በምድራዊ መንግሥት ጥላ ሥር የመጓዝን ዝንባሌ አስወግዶ የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ አደራ የተሰጠውን ሕዝብ ለማገልገል በዓላማው የቆመ ፣ ነፃ ቤተ ክርስቲያንን ለመምራት የተዘጋጀና በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ የሐዋርያት ጉባኤ መሆኑን በተግባር እንዲያረጋግጥ ጉባኤያችን በአጽንኦት ይጠይቃል

፰. ስለምግባረ ሠናይ (በጎ አድራጎት) ድርጅት አወቃቀር ፣ ቤተ ክርስቲያናችንን ስለ ከበቡአት ልዩ ልዩ እምነቶች ፣ በዚህ ሀገር የተወለዱትንና የሚወለዱትን ሕፃናትና ወጣቶችን ስለ ማስተማር ፥ በጉባኤው በምሁራን በቀረቡት ጥናቶች ላይ ተመረኩዘው ጥናት እንዲያካሂዱና ወደተግባር የሚለወጡበትን ንድፍ እንዲያቀርቡ የባለሙያዎች ኮሚቴ ተቋቋቁሞአል። በተለይም እዚህ ሀገር የተወለዱትንና የሚወለዱትን ልጆች ማስተማር ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት የሃይማኖት ፣ የታሪክ ፣ የባህልና የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት እንዲዘጋጁ ፣ ልጆችን የማስተማር ከፍተኛ ልምድ ካላቸው አባል አብያተ ክርስቲያናት ጋራ የልምድ ልውውጥ በማድረግ አንድ ወጥ የትምህርት አሰጣጥ እንዲኖር ጉባኤው ወስኖአል።

፱. እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ከክርስቶስ ልደት ወዲህ ሁለት ሺሕ ዘመንን አጠቃለን ሦስተኛውን ሺህ አንድ ብለን ለመጀመር በዋዜማ ላይ እንገኛለን ፤ በ፫ኛው ሺህ የጉዞ መርከብ ከመሳፈራችን በፊት በሀገራችን ፣ በቤተ ክርስቲያናችንና በማኅበራዊ ሕይወታችን የሚታዩ ችግሮችን ፣ የጥላቻና የግጭትን ፣ የመቃቃርና የመለየትን መንፈስ ከውስጣችን አስወግደን ዕርቅና ሰላምን ፍቅርንና መተሳሰብን በመፍጠር ለልማት ፣ ለእድገት ፣ ለአንድነትና ለብልጽግና ከልብ መዘጋጀት ይኖርብናል ፤ እንዲሁም ለሀገራችንና ለማኅበራዊ ሕይወታችን የማይበጀውን ክፉ አሳበና አሮጌ አመለካከት ሁሉ እንደ እድፍ እንደ ጉድፍ ከኅሊናችን አውጥተን ከአሮጌው ዘመን ጋራ ወደኋላ በመተው የታሰሩት ተፈተው ፣ የተጣሉት ታርቀው ፣ የተራቡት ጠግበው ችግርና ድህነት ከወገኖቻችን ጫንቃ ላይ ወርዶ እንቅፋት በሌለበት የልማትና የአንድነት ጎዳና እጅ ለእጅ ተያይዘን እንድንጓዝ የጉባኤያችን ጥልቅ ምኞትና ጸሎት ነው

## <u>የጉባኤው ማሳሰቢያ</u>

ባለፉት አሥር ዓመታት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ሲኖዶስ ተሰዶአል ፣ ቤተ ክርስቲያን ተሰዳለች ፣ መንበርዋም ተሰዶአል በሚልና ፥ ሲኖዶስ አልተሰደደም ፣ ቤተ ክርስቲያን አልተሰደደችም ፣ መንበርዋም አልተሰደደም በሚል ሁለት ዐይነት አወዛጋቢ ጉዳይ ምእመናን ግራ ስትጋቡ ቆይታችኋል። ዛሬም የቃሉም ሆነ የጽሑፉ መግለጫ በመረረና በከረረ መልኩ ቀጥሎአል። ይህ የቃልም ሆነ የጽሑፍ መመላለስ እናንተን የበለጠ ግራ የሚያጋባ እንጂ የማያስተምር ፣ መለያየትን የሚያሰፋና ጥላቻን የሚያተርፍ እንጂ ወደ ሰላምና አንድነት የማያመጣ ሆኖ ጉባኤያችን አግኝቶታል ፤ አልፎ ተርፎም ቤተ ክርስቲያናችንን ሰድቦ ለሰዳቢ አሳልፎ መስጠት እንደ ሆነ ጉባኤያችንን ይሰማዋል ፤ በዚህም እጅግ ያዝናል። ለዚህም አዛላቂ መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ግራ የተጋባው ሕዝባችን በመረጠው ቦታና ጊዜ ሁለታችንም የጋራ መድረክ አዘጋጅተን በሕዝቡ ፊት በግልጽ እንድንወያይና ከሕዝቡም ለሚቀርቡልን ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እንድንችል በአካል መገናኘት ነው። ስለዚህ ምእመናን ሁላችሁ! ለዚህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያናችን ጉዳይ ትኩረት በመስጠት በየቤተ ክርስቲያናችሁ በሁለቱም ክፍል ላለነው ወገኖች ጥያቄ እንድታቀርቡ ፣ የውይይቱንም መድረክ በማዘጋጀት እንድትተባበሩ ጉባኤያችን አደራ ጭምር ያሳስባል። የውይይቱ መድረክ አዛላቂ ሰላምና እርቅን ሊያመጣ ፣ እውነቱም የት ላይ እንዳለ ለምእመናኑ በቂ ትምህርት ሊሰጥ የሚችል ብቸኛ አማራጭ መሆኑን ጉባኤያችን በጽኑእ ስለሚያምን ለዚህ የውይይት መድረክ መዘጋጀት ቅድሚያ ሰጥቶ የሚሠራ መሆኑንም ያረጋግጣል።

የሰላም አምላክ እግዚአብሔር ሀገራችንና ቤተ ክርስቲያናችንን በሰላም በአንድነት ይጠብቅልን አሜን።

***<u>በጉባኤው የተካፈሉ አብያተ ክርስቲያናት ዝርዝር</u>***

፩. ርእሰ አድባራት ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም ቤ.ክ. ዋሽንግተን ዲሲ
፪. ደብረ ሰላም መድኃኔ ዓለም ቤ.ክ. ሚኒያፓሊስ ሚኒሶታ
፫. አዲስ ዓለም ጽዮን ማርያም ቤ.ክ. ታምፓ ፍሎሪዳ
፬. ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ቤ.ክ. አትላንታ ጆርጂያ
፭. ደብረ ምሕረት ቅዱስ ሚካኤል ቤ.ክ. ዳላስ ቴክሳስ
፮. ደብረ ገነት ዐማኑኤል ቤ.ክ. ፔንሴልቫኒያ ፊላዴልፊያ
፯. ደብረ ሣህል በኣታ ለማርያም ቤ.ክ. ኒውዮርክ
፰. ደብረ መድታኒት መድኃኔ ዓለም ቤ.ክ. ኒውዮርክ
፱. መካነ ብርሃን ቅድስት ሥላሴ ቤ.ክ. ሻርለት ሰሜን ካሮላይና
፲. ደብረ ገነት በኣታ ለማርያም ቤ.ክ. ሂውስተን ቴክሳስ
፲፩. ደብረ ሰላም ቅዱስ ገብርኤል ቤ.ክ. ኮሎምቦስ ኦሃዮ
፲፪. ምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ቤ.ክ. ፖርትላንድ ኦሪጎን
፲፫. ደብረ ገነት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤ.ክ. ሚሽጋን